## Social፡ ጎርፉና ያስከተለው ጥፋት





ፕ/ት ግርማ ወልደጊዮርጊስ　　　አቶ ንጉሱ አክሊሉ

ተፈጥሮን በመንከባከብ ለአካባቢው ልማትና ሕይወት መሰረት እንዲሆን የማድረጉን ሥራ በበለጠ አጠናክሮ መቀጠል የአሁኑ ትውልድ፣ የምሁሩና የኅብረተሰቡ ኃላፊነትና ግዴታ መሆኑን አቶ ግርማ ወልደጊዮርጊስ የኤፌዴሪ ፕሬዚዳንት አስታወቁ፡፡

በመላ ሀገሪቱ ላይ የተከሰተውን የጎርፍ አደጋ አስመልክቶ ታህሳስ 4 ቀን 1999 የተካሄደውን አውደ ጥናት ፕሬዚዳንቱ በንግግር ሲከፍቱ እንዳመለከቱት ሰው ካሰበና ከሰራ ተፈጥሮ በጣም ክፉ አይደለችም፡፡ ግን ተፈጥሮን ዝም ካላት መሃሪ ልትሆን አትችልም፡፡

ስለሆነም እየተደጋገመ ጥፋት ሲከሰት የሚመጣውን መጠበቅ፣ የተሻለ መከላከያ መገንባትና ጥፋቱ እንዳይኖር ማድረግ ከሰው አቅም ውጭ እንዳልነበረ አስረድተዋል፡፡

በአገራችን ውሃን መቆጣጠር አለመቻላችንና መሬትንም ማጥፋታችን የሚያሳዩ ምልክቶች እየጎሉ መጥተዋል ያሉት ፕሬዚዳንት ግርማ ለዚህም ማስረጃው በአንድ ወቅት ባሕር የነበረው ሀሮሚያ አሁን የእርሻ ሜዳ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የኤሌክትሪክ አገልግሎት በመስጠት ለአያሌ ዘመናት የታወቀው ቆቃም የሚታረስ ሜዳ እየሆነ መምጣቱን ጠቁመው ለዚህ መንስኤ የደን መጥፋት መሆኑን በመገንዘብ መልሶ ለማልማት ተገቢውን እንቅስቃሴ እንዲደረግ አሳስበዋል፡፡

የድሬዳዋ ጎርፍም ከፍተኛ ጥፋት ሊያስከትል የቻለው አካባቢው በመራቆቱ ወይም ደን አልባ በመሆኑ ነው፡፡ ከሐረር ወደ ድሬዳዋ ሲመጣ ከመጀመሪያው ሸለቆ አልፎ ወደ ሁለተኛው ሸለቆ ሲገባ የሁለቱ ተፋሰሶች ኃይለኛ የጎርፍ አደጋ ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በቀላሉ መገመት ይቻላል፡፡

ተፈጥሮን የመንከባከብ ሥራ በአንዳንድ ቦታዎች በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመው፣ ለዚህም በትግራይ ክልል በመቀሌና በወቅሮ መካከል ያለው መሬት ተፈጥሮን የመንከባከብ ሥራ በአንዳንድ ቦታዎች በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመው ለዚህም በትግራይ ክልል በመቀሌና በወቅሮ መካከል ያለው መሬት ለብዙ ዘመናት በረሃማና ወንዙም ደረቅ ነው ተብሎ የተተወ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡ ይሁን እንጂ መሬቱ እንዳይታረስ በማድረግና መጠነኛ ችግኞችን በመትከል በአሁኑ ጊዜ ለምቶ ወንዙም ውሀ የማይታይበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አቶ ንጉሱ አክሊሉ የአካባቢ ተቆርቋሪዎች መድረክ አስተባባሪ አውደ ጥናቱ የተዘጋጀው በመላ ሀገሪቱ በቅርቡ ተከስቶ የነበረውን ጎርፍ መንስኤ ለይቶ ለማወቅ፣ ያስከተለውም ጉዳት በዝርዝርና በጥልቀት ለመረዳትና ይህ አይነቱ ጥፋት ዳግም እንዳይከሰት ለማድረግ የሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማመንጨት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

አካባቢን በሚገባ ካልተንከባከቡትና ካልጠበቁት ቀጣይነት ያለውን ልማት ማምጣት የማይታሰብ ነው፡፡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የመሬት መራቆት ያስከተለው የጎርፍ አደጋ ቀጣይነት ያለውን ልማት

ለማምጣት በሚካሄደው እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። በዚህ አይነት ሁኔታም የምእተ ዓመቱን ግብ ማሳካትና ድህነትን የመቀነስ ሥራ አስቸጋሪ እንደሚያደርገው አቶ ንጉሱ አስታውቀዋል።

አቶ ስለሺ ካሳዬ የድሬዳዋ ከተማ ነዋሪ ጎርፉ ባስከተለው አደጋ ከጉዳት በተረፉ ወገኖች ስም ሆነው እንዳብራሩት፣ ሐምሌ 30 ቀን 1998 ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ሳቢያ በውሃ ተወስደው የሞቱት ሰዎች አስክሬን በ100 ወይም በ200 ይቆጠር እንጂ ያልተገኘው አስክሬን ከዚህ በላይ እጥፍ ድርብ እንደሆነ ተናግረዋል።

እንጦጦ ከሚገኘው ከጉራጌ ሰፈር እስከ ሸኔሌ ድረስ በእግር ተጉዘው በርካታ አስክሬን በየቦታው ወድቆ ማየታቸውን፣ ከዚያም ድል ጮራ ሆስፒታል ሲሄዱም እንደዚሁ ብዛት ያለው አስክሬን ተከማችቶ መመልከታቸውን አስረድተዋል።

በድሬዳዋ ከ1930 እስከ 1998 ድረስ በየወቅቱ ከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተከስቶ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ጥፋት ማስከተሉን አመልክተው በተለይም መጋቢት 22 ቀን 1973 የደረሰው ጎርፍ የአዲስ ከተማን አካባቢ፣ ፍልውሃን፣ ግንፍሌ፣ ኮኮ ቀበሌን አጥለቅልቆ ተሽከርካሪዎችን ጠራርጎ መወሰዱንና እኩሌታዎቹን ደግሞ እዚያው ቀብሮ ያስቀራቸው መሆኑን ገልጸዋል።

የጎርፉ መጠን በየደቂቃው እየጨመረ መጥቶ በቤተመንግሥቱ ግንብ አልፎ፣ የከዚራን ድልድይ አናግቶና በድልድዩ ላይ አልፎ ወደ ከዚራ በመዝለቅ ባቡር ጣቢያ ደረሰ። እንደገና የኋሊት ተመልሶ ወደ ነምበርዋን በማቅናት ላይ እንዳለ ኖቶርዳም ትምህርት ቤት ሲደርስ አቅም አነሰውና ቀረ።

በዚህም ሳይበቃ እንደገና ደግሞ ሁለተኛው ጎርፍ ሌሊት መጣ። በቀን ከመጣው ጎርፍ ለማምለጥ ንብረታቸውን ወደ ውጭ አውጥተው የነበሩ ሰዎች ንብረታቸውን ለመጠበቅ ምሽቱን በቦታው ላይ ቆመው ነበር። ሰው ከዚህ አደጋ ለመከላከል ወደ ኮረብታማ ሥፍራ ለመውጣት ተገደደ። ሌሊት የመጣው ጎርፍ ከቀኑ የባሰ ስለነበር የድሬዳዋ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ሁለት መጋዘኖችን ሰብሮ በመግባት በውስጣቸው የተከማቸውን የጥጥ ቦንዳ እያንከባለለ እስከ ሸኔሌ ድረስ ወስዶ ጥሏል። በወቅቱም በጎርፍ ለተጎዳው ሕዝብ ምንም ዓይነት ዕርዳታ አልተደረገለትም።

ከአቶ ስለሺ ማብራሪያ ለመረዳት እንደተቻለው ድሬዳዋን ጎርፍ አጥለቀለቃት፣ ብዙ ሰውም ወሰደ፣ ንብረት ወደመ እየተባለ የሚሰማው ሮሮ መፍትሄ ሊያገኝ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ከአዲስ አበባና ከአዋሳ ዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ስምንት ተመራቂዎች በፎገራ ፕሌንስ፣ በኦሞ ጊቤና፣ በአዋሽ ተፋሰሶች፣ እንዲሁም በድሬዳዋ ጎርፉን አስመልክተው ባካሄዱት ምርምር የደረሱባቸውን ውጠ ቶች በየተራ አቅርበዋል። ካቀረቧቸው የምርምር ውጤቶች በፎገራ ፕሌንስ እ.ኤ.አ ከ1996 እስከ 2006 ድረስ ስምንት ጊዜ የጎርፍ አደጋዎች ተከስተዋል። በ1996 በደረሰው አደጋ 40 ሰዎች ሲሞቱ ወደ 16 ሺህ የሚጠጉ ሰዎች ተፈናቅለዋል።

እ.ኤ.አ በ2006 በተከሰተው የጎርፍ አደጋ ደግሞ 35 ሺህ ሰዎች ተፈናቅለው ሦስት ሰዎች ሞተዋል። 6 ሺህ 673 ሄክታር መሬት ላይ የነበረና 70 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ ልዩ ልዩ አይነት ሰብል ወድሟል። በዚሁ አካባቢ ከ200 ሺህ በላይ ሰዎች እንደሚገኙ ከእነዚህም መካከል 80 በመቶ ያህሉ ነዋሪነታቸው በገጠር እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በኦሞ-ጊቤ ተፋሰስም ካለፉት 20 ዓመታት ጀምሮ የዝናቡ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ መቀየሩን በተለይም በታችኛው ኦሞ ጎርፍ አዲስ ክስተት አለመሆኑን የጥናቱ አቅራቢዎች አመልክተዋል። ለጎርፉ መከሰት ምክንያቱ የአካባቢ መራቆት ወይም የዝናብ መኖር ብቻ አይደለም። በማኅበራዊ ኢኮኖሚ ልማት ላይ የተሳሳተ አስተዳደር መኖርና የመንገድ ግንባታ ለጎርፉ መከሰት አስተዋጽኦ አበርክቷል። በዚህም አደጋ በዳሰነች ወረዳ ብቻ 364 ሰዎችና 3000 ከብቶች ሲሞቱ 18 ሺህ ሰዎች ተፈናቅለዋል።

በአደጋው በ24 ሄክታር ላይ የነበረውና 6 ሚሊዮን ዩ.ኤስ. ዶላር የሚያወጣ የአበባ እርሻ ወድሟል፡፡

በድሬዳዋ አካባቢ ደግሞ እ.ኤ.አ ከ1945 እስከ 2006 ድረስ ዘጠኝ ጊዜ የጎርፍ አደጋ ደርሷል፡፡ እ.ኤ.አ በ2006 በተከሰተው አደጋ 256 ሰዎች ለህልፈተ ህይወት መዳረጋቸውን፣ 244 ሰዎች መጥፋታቸውንና 3427 ሰዎች ደግሞ መፈናቀላቸውን ተገልጿል፡፡ በመስኩ የተካሄደው ጥናት እንደሚያሳየው የሞቱት፣ የጠፉትና የተፈናቀሉት ሰዎች ቁጥር በይፋ ከተገለጸው በእጅጉ ይበልጣል፡፡

በታደሰ ገብረማርያም

Posted on Sunday, December 17 @ 13:14:04 EAT by staff